የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፶፯
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፪ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No. 57
ADDIS ABABA May 20th 2011


## ማውጫ


ደንብ ቁጥር ፪፻፴፰/፪ሺ፫
የዲላ ዩኒቨርሲቲ እንደገና ማቋቋሚያ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ……ገጽ ፭ሺ፰፻፷


## CONTENTS


Regulation No.238/2011
Dilla University Re-establishment Council of Ministers Regulation …… Page 5860


### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፴፰/፪ሺ፫
### ዲላ ዩኒቨርሲቲን እንደገና ለማቋቋም
### የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አን ቀጽ ፭ እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ አንቀጽ ፭(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ ‹‹የዲላ ዩኒቨርሲቲ እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፴፰/፪ሺ፫” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

፪. **መቋቋም**

፩/ ዲላ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ ‹‹ዩኒቨርሲቲ›› እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል፡፡

፪/ የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

፫/ ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፲/፪ሺ፫ መሠረት ይተዳደራል፡፡

፫. **ዋና ግቢ**

የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ ዲላ ከተማ ሆኖ በሌሎች ( ታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 238/2011
### COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE RE-ESTABLISHMENT OF THE DILLA UNIVERSITY

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 5 (1) of the Higher Education Proclamation No. 650/2009..

1. ***Short Title***

This Regulation may be cited as the “Dilla University Re-establishment Council of Ministers Regulation No. 238/2011”

2. ***Establishment***

1/ The Dilla University (hereinafter the “University”) is hereby re-established as an autonomous higher education public institution having its own legal personality.

2/ The University shall be accountable to the Ministry of Education.

3/ The University shall be governed by the Higher Education Proclamation No. 650/2009 and the Federal Universities Council of Ministers Regulation No. 210/2011.

3. ***Main Campus***

The University shall have its main campus at Dilla and may establish elsewhere other academic units and centers of research and community services.

## ፬. የተሻረ ደንብ

የዲላ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፳፱/፲፱፻፺፱ በዚህ ደንብ ተሽሯል።

## ፭. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ግንቦት ፲፪ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

## 4. Repealed Regulation

The Dilla University Establishment Council of Ministers Regulation No. 129/2006 is hereby repealed.

## 5. Effective Date

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 20th day of May, 2011.

*MELES ZENAWI*

*PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት